# መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)

ALL ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT ( M E' I S O N E )

P.O.Box 3198 - 10364 Stockholm 3 - Sweden - e-mail: meisone@t-online.de


የካቲት 27 ቀን በተካሄደው የህብረቱ አመራር ቴሌ ኮንፈራንስ በተጠየቀው መሰረት

## ስለ መጭው ምርጫ ከመኢሶን የቀረበ የውይይት መንደርደሪያ ሰነድ

### መግቢያ

መጭውን ምርጫ ካለፈው የተሻለ መቀመጫ ለማግኘት እንንቀሳቀስ፤ ይህ ቁጥር ደግሞ በቀጣዩ በ2002 ዓ.ም . ምርጫ ከጨመረ. ይህ ደግሞ በ2007ቱ ከፍ ካለ...የሚል የአባይን በጭልፋ አካሄድ መያያዝ የለብንም። አንዳንድ ወገኖቻችን የትግሉን መሳካት ወይም አለመሳካት በዚህ መለኪያ ለመመዘን የሚቃጣቸው ስለሚመስል በጉዳዩ በጣም ግልፅ መሆን ያስፈልጋል። በየአምስት አመቱ የምናሸንፈው መቀመጫ ቁጥር በአምስትም አስርም ከመቶ እየጨመረ እንዲሄድ የሚለው ስትራቴጂ የነዚህ ወገኖች ብቻ ሳይሆን የነአቶ መለስም ስሌት ነው። ባለፈው ምርጫ በመንደር ካድሬዎቹ ግፊት ተጥለቅልቀው ታልፈው ባይሄዱ ኖሮ የኢህአዴግ መሪዎች ለተቃዋሚ ድርጅቶች አርባም አምሳም መቀመጫ መልቀቅ ምንም የሚገዳቸው ነገር አልነበረም። እንዲያውም "መድበለ ፓርቲ ስርአት" ለሚለው ፕሮፓጋንዳ የተሻለ ሁኔታ ይፈጥርላቸው ስለነበር ባለን ተጨባጭ መረጃ በወቅቱ እንዲህ አይነቱ "የኮታ" ፖለቲካ እንደነበራቸው እናውቃለን። በመሆኑም በቀጣዩ ምርጫም ተቃዋሚዎች አሁን ካላቸው መቀመጫ አራት አምስትም እጥፍ ከዚያም በላይ አምጥተው ሃምሳም ስልምሳ መቶም መቀመጫ ቢያመጡም ለወያኔ "መድበለ ፓርቲ" ፕሮፓጋንዳ ጥርጊያ ጎዳና ከመስጠት አልፎ ለኢትዮጵያ ህዝብ የነፃነት ተጋድሎ ምንም ፋይዳ ስለማይኖረው ተቃዋሚዎችን የሚያስፈነድቅ "ድል" አይሆንም።

ይህንን ስንል ምርጫ ውስጥ ከተሳተፍን አይቀር መቀመጫ በብዛት ለማሸነፍ እንንቀሳቀስ ማለት አይደለም። ማለት የምንፈልገው ከኛ ይልቅ ኢህአዴግ ይበልጥ ሊነግድበት ለሚችለው የመቀመጫ ድል ብዙ ሳንጨነቅ ትኩረታችን የምርጫው ሂደት ላይ መሆን አለበት ነው። ይህ ምን ማለት ነው?

አንደኛ በሂደቱ ላይ እናተኩር ማለት ወያኔ/ኢህአዴግ ከዚህ ምርጫ በአሸናፊነት ወጣሁ ለማለት ከፈለገ ካለፉት ምርጫዎች ሁሉ ይበልጥ አይን ባወጣ ሁኔታ በገፍና "በኢንደስትሪ ደረጃ" አጭበርብሮ፤ በፖለቲካ ክስረቱ በኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ በአለም አቀፍ ኮሙኒቲው ፊት ሙሉ በሙሉ መጋለጥን መርጦ ብቻ እንዲሆን መስራት ያስፈልጋል ማለት ነው።

ሁለተኛ ሂደቱ ላይ እናተኩር ማለት ወያኔ/ኢህአዴግን እዚህ ክስረት ደረጃ ካደረስነው በሽፍጡ ማግስት "ምርጫው ተጭበርብሯል ውጤቱን አንቀበልም" በሚል ተቃውሟችንን አስመዝግበን ይህንን ምእራፍ እስከ 2002 ዓ.ም. ምርጫ ሳለመዝጋትና በሰርብያ፤ በጆርጂያና በሌሎችም አገሮች እንደታየው ህዝባዊ ትግሉ እርቃኑን ለቀረው ኢህአዴግ ምንም ፋታ ሳይሰጥ ስለሚቀጥልበት ሁኔታ ህዝባችንን ከወዲሁ በግልፅ ማዘጋጀት ይኖርብናል ማለት ነው።

ሶስተኛ ሂደቱ ላይ እናተኩር ማለት ይህ ስትራቴጂያችን ሙያ በልብ ተብሎ በድርጅቶች አባላትና አመራሮች አካባቢ ብቻ ሳይወሰን መላው ህዝባችን፤ እንዲሁም የሃገራችን ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች አላማችን ገብቷቸውና አምነውበት ትግሉን እንዲያፋፍሙ፤ ወያኔ ኢህአዴግም ቢሆን ምርጫውን ቧልት አርጎ እንዳይወስደው፤ አለም አቀፍ ኮሙኒቲውም በዚች አገር እምነት ሊጣልበት የሚገባውና ሃላፊነት የሚሰማው አማራጭ ሃይል እንዳለ እንዲያውቅ "ለሚመለከተው ሁሉ" ከወዲሁ በግልፅ መቀመጥ ይኖርበታል ማለት ነው።

ግን ደግሞ እዚህ የትግል ደረጃ ለመድረስ ብዙ ድፍረት፤ ብዙ ጥራት፤ ብዙ የፈጠራ ችሎታን የሚጠይቁ በርካታና አጣዳፊ ተግባራት ከፊታችን ተደቅነዋል። ዛሬ እነዚህን ተግባራት ወቅቱ በሚጠይቀው ቅልጥፍና እያከናወንን አይደለንም። ለዚህ ዋናው ምክንያት ምርጫውንና ለዴሞክራሲ የሚደረገውን የጋራ ትግል በተመለከተ ለብዙ ቁልፍ ጥያቄዎች ጥርት ያለ መልስ መስጠት አለመቻላችንና እንዲያውም በነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ ልዩነቶች መኖራቸው ነው። ባለፈው በማርች ስድስቱ ቴሌ ኮንፈራንስ እንደታየው ከሆነ መጭው ምርጫ ውስጥ ስለመሳተፋችንና ስላለመሳተፋችን እንኳን ሁላችንም ተመሳሳይ አቋም የለንም። ህብረቱ የሚያሰልፋቸው ተወዳዳሪዎች የማን እጩዎች ይሆናሉ? በሚለው ጥያቄ የተለያዩ መልሶች አሉን። በምርጫ አሸንፈን ይህንን መንግስት እንተካለን ብንልም ምን ተልእኮ ያለው መንግስት ነው የምናቋቁመው በሚለው ጥያቄና ህዝብ ፊት ይዘን ስለምንቀርበው አማራጭ የመንግስት ፕሮግራም ምንም የሚወራ ነገር የለም። ይህ በድምሩ ሲታይ ህብረቱ ትልቅ ውዥንብር ውስጥ እንዳለ ያመለክታል።

ከዚህ በመነሳት የህብረቱ አመራር ያለው ውኸንብር ካልጠራ ትግሉ አሁን ካለበት አደገኛ የመፍዘዝ ሁኔታ ሊ ወጣ እንደማይችል በመገንዘቡ በአስቸኳይ በነዚህ ነጥቦች ላይ ውይይት እንዲደረግ ወስኗል። የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊ ስት ንቅናቄ (መኢሶን) ለዚህ ውይይት መንደርደሪያ እንዲሆን አንድ አቅጣጫ ሰጭ ሰነድ አሰናድቶ እንዲያቀርብና አባ ል ድርጅቶች እንዲወያዩበት በህብረቱ አመራር በተጠየቀው መሰረት እስከ ግንቦት 1997 እ.ም.ና ከዚያም ባሻገር መከተ ል ስላለብን አካሄድ ያለንን ሃሳብ እንደሚከተለው ለውይይት እናቀርባለን። ይህንን ስናደርግ በመሰረቱ ባለፈው ሃምሌ ወር ለህብረቱ መመስረቻ ጉባኤ ካቀረብነው ሰነድ የተለዩ ሃሳቦች ለማቅረብ አንሞክርም። አላማችን በዚያ ሰነድ የሰፈ ሩትን ሃሳቦች ለማጠናከርና በቀረው አጭር ጊዜ በአጣዳፊ ተንቀሳቅሰን ብሄራዊ ግዴታችንን እንድንወጣ ስለሆነ አሁን በምናቀርበው ሰነድ ላይ የድርጅቶች አባላት ሲወያዩ ከሃምሌው ወር ሰነዳችን ጋር እያገናዘቡ እንዲመለከቱልን እንጋብ ዛቸዋለን።

## 1. ካለፈው ምርጫ ድርብ ሽንፈት ስለምንቀስማቸው ትምህርቶች

የምንወጣቸው ድክመትችም ሆኑ ዛሬ መደገም የሌለባቸው ስህተቶች በወያኔ "አሸናፊነት" በተጠናቀቀ ማግስ ት እንደ አልባሌ ፋይል በዘጋንው የ1992 ዓ.ም. ምርጫ ልምድ ተንፀባርቀው ስለሚገኙ ይህን የትግል ልምድ ባጭሩም ቢ ሆን ዘወር ብሎ መቃኘት ያስፈልጋል።

ባለፈው ምርጫ ተቃዋሚ ድርጅቶች ድርብ ሽንፈት ደርሶባቸዋል። የመጀመሪያው ግልፅ ሽንፈት በፓርላማ ው ውስጥ ያገኙት መቀመጫ እዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑ ነበር። ሁለተኛውና ዋናው ሽንፈት ህዝባችን በሚልዮን እየ ተቆጠረ ተንቀሳቅሶና ብዙ መስዋእትነት ከፍሎ ትግሉ ከተቀጣጠለ በሁዋላ ይህ ህዝባዊ ማእበል በምርጫው ማግስት እ ንዲከስም በመደረጉ የደረሰብን ሽንፈት ነው። በመጀመሪያውና በውጤት ደረጃ የደረሰውን ሽንፈት በወያኔ ፀረ ነፃ ም ርጫ ርምጃዎች አላክኮ በቀላሉ መሸንት ይቻል ይሆናል። ለሁለተኛውና በሂደት ደረጃ ለደረሰው ሽንፈት ግን ከሁሉም በላይ ተጠያቂዎቹ የተቃዋሚ ድርጅቶች አመራሮች እንደሆኑ መቀበል ያስፈልጋል። ይህ ካልተደረገና ሁሉንም ወያኔ ላይ ብቻ ለመለጠፍ ከተሞከረ ካለፈው ትግል ትምህርት ቀስሞ ወደ ፊት መራመድ አይቻልም።

ባለፈው ምርጫ 540 መቀመጫ ላለው የኢህአዴግ ፓርላማ ተቃዋሚ ድርጅቶች ያቀረቧቸው ተወዳዳሪዎች ተደምረው 140 የማይሞሉ ስለነበር የመንግስት ለውጥ የሚደረግበት ምንም ተአምር አልነበረም። ምርጫው እያንዳን ዱ ተቃዋሚ ድርጅት "የበኩሉን" የቻለውን ያህል በመጭው ፓርላማ ውስጥ ወንበር ለማግኘት የጣረበት በዚህም የተነ ሳ መቀመጫ ውጤት ላይ ያተኮረ ትግል ነበር። ሆኖም ተቃዋሚ ድርጅቶች አምስት በመቶ እንኳን ሳያገኙ ምርጫው በእህአዴግ "የማያወላዳ" ድል ተጠናቀቀ።

ነገር ግን ያለፈው ምርጫ በሃገራችን ለዴሞክራሲ ለሚደረገው ትግል ምንም የረባ አስተዋፅኦ ሳያደርግ አል ፏል የምንለው በመቀመጫ ደረጃ የተገኘው ውጤት ኢምንት በመሆኑ አይደለም። የደረሰው ትልቅ ኪሳራ እዚህ "ሽን ፈት" ላይ ስናተኩርና የተከሰተውን ሽፍጥ ለማጋለጥ ላይ ታች ስንል በሂደቱ ደረጃ ተቃዋሚዎች የተጎናፀፉትን ህዝባዊ ድል ተገቢ ትኩረት አለመስጠታችን ነበር። ይህ ጉዳይ ግልፅ ካልሆነልን ስህተቱ እንደገና ተደግሞ መጭውንም ምር ጫ ያልረባ ግርግር ሊያደርገው ስለሚችል በዚህ ጥያቄ ያለንን ትንተና በአጭሩ አስቀምጠን እንለፍ።

ኢህአዴግ ተጎናፀፈ የተባለው ድል የህገ መንግስትና የምርጫ ጉዳይ ኤክስፐርቶች "ብሬዥኔቫዊ" ብለው የ ሚጠሩት በስልጣን ላይ ያለውና የምርጫውን ሂደት ከዳር እስከዳር የሚቆጣጠረው መንግስት ከዘጠና ከመቶ በላይ መ ቀመጫዎችን ተቆጣጥሮ የሚወጣበት "የማያወላዳ" ድል ነው። ግን ደግሞ "ብሬዥኔቫዊ" የሚባሉት የምርጫ ክስተቶ ች ምልክታቸው የሚያስገኙት ውጤት ብቻ አይደለም። የምርጫዎቹ ካምፔይንም ምንም አይነት እንቅስቃሴ የማይታይ በት ህዝቡም ምንም የረባ ምርጫ በሌለበት ሁኔታ ነገሩን እንደ መብት ሳይሆን እንደ ግዴታ ወስዶ ያገባኛል፤ ጉዳየ ነ ው ሳይል የሚሳተፍበት አሰልቺና ፈዛዛ ሂደት ነው።

በኛ አገር የተካሄደው ምርጫ ከዚህ አንፃር ሲታይ ትልቅና አስገራሚ የሆነ ፓራዶክስ የተንፀባረቀበት ምርጫ ነበር። በውጤቱ እንጂ በሂደቱ "ብሬዥኔባዊ" አልነበረም። ምናልባት በምርጫዎች ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ "ብሬዥኔ ቫዊ" የምንለው ድል የተገኘው "ምርጫ ምን ዋጋ አለው?" ብሎ ከወዲሁ እጁን በሰጠ ህዝብ ላይ ሳይሆን ዜጎች በሚ ልዮን እየተቆጠሩ ተንቀሳቅሰው ከፍተኛ መስዋእትነት በከፈሉበት ሁኔታ ነበር።

ተቃዋሚ ድርጅቶችና ግለሰብ ተወዳዳሪዎች ለምርጫው ለመመዝገብ በመቶ ሸህ የሚቆጠሩ የድጋፍ ፊርማዎች አግኝተዋል። በኢህአዴግ ቁጥጥር ስር ባለች አገራችን ዜጎች በይፋ ፊርማ እየሰጡ ለተቃዋሚዎች ድጋፍ ማሳየት በዋሽንግተን፤ ለንደን ወይም ፓሪስ አውራ ጎዳናዎች "ፒቲሽን" እንደመፈረም አይነት ቀላል ነገር አልነበረም። በዚህ ደረጃ ባሳዩት "ድፍረት" ብቻ ብዙ ወገኖቻችን ይህ ነው የማይባል መከራና ወከባ እንደደረሰባቸው እናውቃለን። በምርጫው እንቅስቃሴ ሳቢያ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያውያን በኢህአዴግ ካድሬዎች ታስረዋል፤ ተገድለዋል፤ ከስራ ተባረዋል፤ ቤት ንብረታቸው ተቃጥሏል፤ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው ተነቅለዋል፤ ርሃብተኞች የተቃዋሚ ደጋፊ ተብለው የምግብ ርዳታ ተነፍጓቸዋል ወዘተ.

የኢህአዴግ መንግስት ዋና ፍላጎት ይህ ማንም ባልጠበቀው ሁኔታ የተቀጣጠለው የህዝባዊ ትግል ምእራፍ ባስቸኳይ እንዲዘጋለት ነበር። የኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ደግሞ በምርጫ ማግስት በሚገኘ የመቀመጫ ልክ ረክቶ ወይም ደግሞ " ይህ ምርጫ ከዳር እስከዳር ተጭበርብሯል" በማለት ተቃውሞን አስመዝግቦ ይዚህን ህዝባዊ ማእበል ፋይል መዝጋት አልነበረም። ይህንን ወያኔ በማጭበርበር ያስመዘገበውን የውጤት ድል እኛ ደግሞ በመስዋእትነት ባስገኘነው ህዝባዊ ማእበል ሂደት ተመርኩዞን ማጋለጥና መዋጋት መቀጠል እንደነበረብን ዛሬ ግልፅ ነው። ነገር ግን ይህ ትክክለኛ አካሄድ በተግባር እንዳይተረጎም በወቅቱ ገና ያልተወጣናቸው ብዙ ግልፅና ዛሬ መደገም የሌለባቸው ድክመቶች ነበሩ።

አንደኛ ይህ ሰፊ ህዝባዊ እንቅስቃሴ በአገር አቀፍ ደረጃ የተቀነባበረና የሚተጋገዝ አልነበረም። ሁሉም በጀግንነት በያለበት የበኩሉን ሲዋደቅ ኢሉባቦር ያለውን ታጋይ ጎንደር ከወያኔ ካድሬ ጋር ከተፋጠጠው ዜጋ፤ አዲስ አበባ የሚንቀሳቀሰውን ሃይል ሃረር ከወያኔ ካድሬ ጋር ከሚዋደቀው ተቃዋሚ፤ አዲግራት ያለው ከአዋሳ፤ ደሴ ያለው ከጂማ የሚተዋወቅበት፤ የሚተጋገዝበት ምንም የጋራ መድረክ አልነበረንም።

ሁለተኛ ትግሉ ከግንቦቱ ምርጫ ባሻገር ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያስችል ምንም ግልፅና የተቀነባበረ ስትራቴጂ አልነበረም። የዚህ ቀጣይ ስትራቴጂ መጥፋት ችግሩ የምርጫ ሰሞኑ ግርግር ሲያከትም የትግሉ ምሜንትም ወይም ቅስም ተሰብሮ እንደገና የህዝባዊ ትግል ማእበል ለመቀስቀስ ደግሞ እስከ ቀጣዩ ምርጫ ለአምስት አመት የመጠበቅ አደጋ ብቻ አልነበረም። ትግሉ መልሶ ከፈዘዘ በተጠናቀቀው የምርጫ እንቅስቃሴ ወቅት በግንባር ቀደምነት ሲታገሉ ወያኔ ካድሬዎች አይን የገቡ ዜጎችን በያሉበት ለአስከፊ የምርጫ ማግስትና የቂም በቀል አፈና የማጋለጥ አደጋም ነበር።

እነዚህ ሁለት ድክመቶች በሂደት የተከሰቱ እንደመሆናቸው መጠን ያኔ በሚገባ ተንቀሳቅሶ ለማረም ራእዩም፤ አቅሙም፤ ጊዜውም አልነበረም። ነገር ግን ዘግይቶም ቢሆን የእርማት እንቅስቃሴ ተደርጎም ነበር። ትግሉ ካለበት "የመካለል" ድክመት ወጥቶ በያለበት የሚገኙ ታጋዮች " የአንድ ሰፊና አገር አቀፍ ንቅናቄ አካል መሆናቸውን እንዲገነዘቡ"ና፤ ከምርጫው ሂደት ባሻገር ይህ ህዝባዊ ማእበል ስለሚቀጥልበት ስትራቴጂ እንዲወያዩ የኢተፖድህ አመራር አስቸኳይ አገር አቀፍ ጉባኤ እንዲጠራ ሃሳብ አቀርቦ ለዚህም አስፈላጊ የሚሆነው ፋይናንስ ተልኮ ምርጫው አንድ ሳምንት ሲቀረው ይህ አገር አቀፍ ስብሰባ በአዲስ አበባ እየሩሳሌም ሆቴል ተካሂዷል።

ስብሰባው ላይ ከተጋበዙት ጋዜጠኞችና ታዋቂ ዴሞክራት ግለሰቦች ተጨማሪ በምርጫው እንቅስቃሴ ግንባር ቀደም ተሳትፎ ካሳዩት ዜጎች አንድ መቶ ሃያ ያህል ከአዲስ አበባ፤ ከሃረርጌ፤ ከባሌ፤ ከአርሲ፤ ከትግራይ፤ ከወሎ፤ ከኢሉባቦር፤ ከስሜን፤ ከደቡብና ምስራቅ ሸዋ ሲሆኑ ከዋና ዋና ከተዎች ደግሞ ከአዋሳ፤ ከአምቦ፤ ከናዝሬት፤ ከደብረ ዘይት፤ ከወሊሶ፤ ከፍቼና ከጂማ የመጡ ታጋዮች ተገኝው ሁለት ቀናት ተወያዩ። ለቀጣዩ ትግልም በጉባኤው ከተሳተፉት ስምንት ተቃዋሚ ድርጅቶች የተውጣጣ አስተባባሪ ኮሚቴ ተሰየመ።

ነገር ግን ይህ ሙከራ መጀመሪያውኑ በጊዜ ጥበት የተነሳ በቂ ዝግጅት ያልተደረገበት፤ ለቀጣዩ ትግል የሚያስፈልገው የፋይናንስ አቅም ያልተዘጋጀበት፤ በሃገር ውስጥ የሚገኙ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሙሉ ያልተስማሙበት ስብሰባ ስለነበረና ከሁሉም በላይ ደግሞ በሃሳቡ ዙሪያ በቅድሚያ ሰፊ ቅስቀሳ ባለመካሄዱ ህዝባዊ ድጋፍ ስላልነበረው የተመኘነውን ውጤት አላስገኘም።

በተጭበረበረው ምርጫ ማግስት አስተባባሪው ኮሚቴ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በያለበት የተከሰቱትን አይን ያወጡ ፀረ ነፃ ምርጫ ድርጊቶች አጋልጦ የዚህን ምርጫ ውጤት እንደማይቀበለው አስታውቆና "መስፈርቶች በተሟሉበት ሁኔታ በስድስት ወር ውስጥ ሌላ ምርጫ እንዲካሄድ" ጥሪ አድርጎ የ1992 አ..ም. የምርጫ ሂደት በዚሁ ተዘጋ። ወያኔ እንደተጠየቀው በስድስት ወር ውስጥ ሌላ ምርጫ የማዘጋጀቱን ነገር አሻፈረኝ ቢል ምን ይደረጋል? የሚለው ጥያ

ቱ እንኳን ተገቢ መልስ ሊያገኝ ቀርቶ ጨርሶም ስላልተነሳ ከተባለው ስድስት ወር በኃላ መልሶ ያነሳው ማንም አልነበረ ም።

እንደተፈራው የህዝባዊ ትግሉ ቅስም ብዙ ሳይቆይ ተሰበረ፤ የወያኔ ካድሬዎች በካምፔይኑ ወቅት በግንባር ቀደምነት በተንቀሳቀሱት ዜጎች ላይ የቂም በቀል አፈና ውርጅብኛቸውን ተያያዙት፤ የህዝባችን ትግል አመራርም ቅን ብርም ተነፍጎት በያለበት ለወያኔ ጭፍጨፋ ደረታቸውን የሰጡ ግብታዊ ፍንዳታዎች ተበራከቱ....እኛም ከአምስት አመ ት በሁዋላ ይኸው ለ1997 ኢ.ም. ምርጫ ደግሞ ህዝባችንን ተነስ ለማለት እየተዘጋጀን እንገኛለን።

እነዚህን የአገር አቀፍ ቅንብርንና የትግሉን ቀጣይነት ችግሮች በተመለከተ በሃምሌ ብቀረብነው ሰነድ በካም ፔይኑ ወቅት አስፈላጊ ይሆናሉ ስለምንላቸው ተወዳዳሪዎችን በሙሉ ያካካተቱ ሁለት አገር አቀፍ ጉባኤዎችና ከዚያም የትግሉን እምርታ ለመጠበቅ መቋቋም ስለሚገባው "ተተኪ ሸንጎ" ያለንን ሃሳብ ሰንዝረናል። እነዚህ ሃሳቦች አሁንም ቢ ሆን ሁላችንም ለምንመኘው ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ወሳኝ ይሆናሉ የሚል ሃሳብ ስላለን የህብረቱ አባላት እንዲወያዩባቸ ውና ከዚህ ሌላ የተሻለ ስትራቴጂ አለን የሚሉ ድርጅቶች ካሉ ደግሞ ሃሳባቸውን ለውይይት እንዲያቀርቡ እንጋብዛለን ። ከዚህ በተጨማሪ በመጭዎቹ ወራት መከተል ስለሚገባን አካሄድ ያለንን አስተያየት እንደሚከተለው ለውይይት እና ቀርባለን።

## 2. መስፈርቶች ተሟሉ አልተሟሉ ምርጫው እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ ይኖርብናል

በመጭው ምርጫ የመሳተፍ ወይም ያለመሳተፍ ጉዳይ ብዙ ወገኖቻችንን አስጨንቆ የያዘ ከባድ ጥያቄ በመሆ ኑ " መስፈርቶች ከተሟሉ እንሳተፋለን፤ መስፈርቶች ካልተሟሉ አንሳተፍም " በሚል ቀጭንና "ሲምፕሊስቲክ" መል ስ የምንሸኘው ጥያቄ አይደለም። የህብረቱ መለስተኛ ፕሮግራም ኢህአዴግ ሁኔታዎችን አሟልቶ ለውድድር ካልቀረበ ህብረቱ መክሮ ሌላ አቅጣጫ ይቀይሳል የሚል አሻሚ አቋም አሰፍሯል።

በዚህ ጉዳይ ያለው ልዩነት በየካቲት 27ቱ ቴሌ ኮንፈሬንስ ላይ ተንፀባርቋል። በአንድ በኩል በመጨረሻ ው ደቂቃ ምርጫውን ቦይኮት የማድረግ መብታችን እንደተጠበቀ ሆኖ ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ ባይሟሉ እንኳን የምር ጫውን ካምፔይን ቦይኮት ማድረግ የለብንም፤ ባለ በሌለ ሃይላችን ተንቀሳቅሰን ህዝባችንን ለማንቀሳቀስ የቆረጥን መሆኑ ን ከወዲሁ በግልፅና በይፋ ማስቀመጥ ይኖርብናል የሚለው ሃሳብ ተሰንዝሯል። አንዳንድ ተወካዮች ይህንን አስተሳሰብ የማይጋሩ መሆናቸው በግልፅ ታይቷል። እነዚህ ወገኖች " እስካሁን ያለው የህብረቱ አስተሳሰብ ሁኔታዎች እንዲሟሉ መደራደር የሚል ነው። በሌላ በኩል ሁኔታዎች እንዲሟሉ በዲፕሎማሲው መስክ መስራት፤ እንደዚሁም ህዝቡን ማ ንቀሳቀስ አለብን እንጂ ካሁኑ እንሳተፋለን ማለት የለብንም" በማለት ያላቸውን ልዩነት ገልፀዋል።

እንዲህ አይነቱ አቋም ምርጫው ነፃ ካልሆነ ምንም የረባ ውጤት አያስገኝም ከሚል ስሌት ተነስቶ ወሳኝ የሆነ ውን የህዝባዊ ማእበል መቀስቀስ ሂደት የሚረሳ አቋም ብቻ አይደለም። ከሚሰጠው መልስ የሚያስከትላቸው ጥያቄዎ ች ይበልጣሉ። መንግስት መስፈርቶችን መቀበሉ ወይም አለመቀበሉ የሚታወቀው መቼ ነው? ምርጫው ስድስት ወር ሲ ቀረው? አንድ ወር ሲቀረው? እስኪያሟላ መጠበቃችን አውቆ ኢህአዴግ ነገሮችን ሆን ብሎ የማንተት ስትራቴጂ ቢከተ ልስ? ተሟልቷል አልተሟላም ለማለት ሚኒመም የምንቀበላቸውና የማንቀበላቸው ነጥቦች አውጥተናል ወይ? መስፈርቶ ች አልተሟሉም ብለን እኛስ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የጊዜ ገደብ አለን ወይ? መሳተፍ አለመሳተፍ ውሳኔ እስከምንደርስ ባ ለው ጊዜ ተግባራችን ወይም የትግል አጀንዳችን ምንድን ነው? የህዝባችን የነፃነትና የዴሞክራሲ ተስፋ በዚህ ድርድር ውጤት ላይ እንተወዋለን ወይስ መስፈርቶች ካልተሟሉ በደፈናው "ምርጫው" ውስጥ አንሳተፍም ከሚለው ሌላ አማ ራጭና ተጨባጭ የትግል መፈክሮች አሉን? በተሳትፎና በቦይኮት ጉዳይ አሁን ያለው ያልጠራ ሁኔታ በሙሉ ልብ አጣ ዳፊ ተግባራትን እንዳንያያዝ አድርጎን ወርቅማ ጊዜ እየባከነ ስለሆነ ህብረቱ በዚህ ጉዳይ ባስቸኳይ ለሁለት ጥያቄዎች ግልፅ መልስ መስጠት ይኖርበታል።

አንደኛ መስፈርቶች አልተሟሉም ብለን የቦይኮት ውሳኔ ከደረስን ቦይኮት የምናደርገው ምኑን ነው? አጠቃላዩ ን የምርጫ ሂደት ነው ወይስ የመጨረሻዋ ቀን የሚካሄደውን የድምፅ መስጠት ሂደት ብቻ? በኛ ግምት በሁለቱ መካከ ል ትልቅ ልዩነት አለ። የሚያዋጣ የሚመስለን አካሄድ መስፈርቶች ተሟሉ አልተሟሉ የምርጫውን ካምፔይን በምንም

አይነት ቦይኮት አናደርግም ብለን ከተቻለ በአምስት መቶ አርባዎቹ የምርጫ ክልሎች እጩዎች አስልፈን የኢህአዴግን መንግስት ለመፋለም ባስቸኳይ ዝግጅት መጀመር አለብን የሚል ነው።

ሁለተኛ የቦይኮት ውሳኔ ላይ የምንደርሰው መቼ ነው? የቦይኮት ነገር ከመጣ ይህንን የምናደርገው በሚልዮን የ ሚቆጠሩ ወገኖቻችን ጋር አብረንና በካምፔይኑ ወቅት የተፈፀሙትን ፀረ ነፃ ምርጫ እርምጃዎች በሙሉ በመአከል ደረ ጃ መዝግበንና በህዝባችንና በአለም አቀፉ ኮሙኒቲው ፊት አጋልጠን እንጂ ከህዝባችን ተነጥለን ብቻችንን መሆን የለበ ትም። ይህ ደግሞ ከካምፐይኑ ማብቂያ ላይ ድምፅ ለመስጫው ቀን ሳምንትም ሆነ ሃያ አራት ሰአት ሲቀረን ባጭሩ በ መጨረሻዋ ደቂቃ የምንወስነው ነገር መሆን ይኖርበታል። ከዚህም አልፎ መሄድ ይቻላል። የምርጫው ሂደት በካምፔ ይኑ ወቅት ብቻ ሳይሆን የምርጫው እለት በተጨባጭ በሚፈፀሙ ፀረ ነፃ ምርጫና ህገ ወጥ ድርጊቶችና ማጭበርበሮች ሙሉ በሙሉ ሊበከል እንደሚችል ባለፈው የምርጫ ወቅት አይተነዋል። በመሆኑም ህዝባችንን በሚልዮን አንቀሳቅሰን ፤ ለቀጣዩ ትግል ተዘጋጅተን እስከተገኘን ድረስ በዋዜማው ዊዝድሮው ከማድረግ እስከ ድምፅ መስጠቱ ሂደትም ድረስ ተሳትፈን በእለቱ የተፈፀሙ ህገ ወጥ ድርጊቶችን አጋልጠን ውጤቱን እውቅና አንሰጠውም የሚል አቋም በምርጫው ማግስት አስተጋብተን እንደ ጆርጂያና ሰርብያ ትግላችንን መቀጠል እንችላለን።

በዚህ ነጥብ ስምምነት ከተደረሰ ሰፍር ቁጥር የሌላቸውና እጅግ አጣዳፊ የሆኑት ተግባሮቻችን ከፊታችን ስለ ሚደቀኑ በአልሆነ አቅጣጫ በመኳተን በእርግጥ የእኛንም የእትዮጵያን ህዝብም ወርቅማ ጊዜ እያባከንን እንደሆነ ወዲ ያውኑ ከፀሃይ ደርቶ ይታየናል። ከነዚህ መእት ተግባራት አንፃር ሲታይ አንዱ አጉል ትኩረት የምንለው ለነፃ ምርጫ እ ኛ ራሳችን ማሟላት ያሉብንን ቅድመ ሁኔታዎች "ለጊዜው" ወይም "ወያኔ/ኢህአዴግ የበኩሉን እስኪያሟላ" በሚል አ ካሄድ ችላ ብለን ከመንግስት ጋር ለሚደረገው ድርድር እየሰጠን ያለነው ስፍራ ይመስለናል።

### 3. መስፈርቶች እንዲሟሉ ከመደራደር መታገልን እናስቀድም

የነፃ ምርጫ መስፈርቶች ስለሚሟሉበት ሁኔታ ከመንግስት ጋር መደራደር አያስፈልግም አንልም። የኢህአዴግ መንግስት አለም አቀፋዊ መስፈርቶችን እንዲያሟላ መታገል ያስፈልጋል። ሆኖም ይህንን በአሁኑ ሁኔታ "በሃገሪቱ ታሪ ክ ለመጀመሪያ ጊዜ መንግስት ከተቃዋሚዎች ጋር ውይይት ከፈተ" በሚለው ነጥብ እንዲያውም ከኛ ይልቅ ኢህአዴግ እየተጠቀመበት ያለውን "ድርድር" ከሚገባው በላይ ትኩረት ሰጥቶ ሌሎች አጣዳፊ ተግባራትን መዘንጋት አያስፈልግም ። ለምን?

አንደኛ ከመንግስት ጋር የሚደረገው ድርድር በዝግ ችሎት መልክ ሳይሆን ህዝቡም እንዲገባበት ለማድረግ መ ሰረታዊ የሆኑትን ጥያቄዎቻችንን በቀላል ቋንቋና በነጥብ በነጥብ አስቀምጠን ከካምፔይኑም በፊት ሆነ በካምፔይኑ ወቅ ት የመራጩ ህዝብ መቀስቀሻ መሳሪያ እንድናደርጋቸው ያስፈልጋል። ይህንን ካደረግን በምርጫው ካምፔይን ወቅት በ ሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በወያኔ ካድሬዎች በያለበት የሚፈፀሙትን ፀረ ነፃ ምርጫ ድርጊቶች ለመዋጋትና ለማጋለጥ የሚያስችላቸው መሳሪያ ሰጠናቸው ማለት ነው። ለነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ከኢህአዴግ ጋር ተደራድረን ከምናገኘው 'ዋስ ትና' ይልቅ በዚህ መልክ የህዝባችን ንቁ ተሳትፎ ሺ ጊዜ ይበልጥ አስተማማኝ ውጤት ይሰጣል የሚል ፅኑ እምነት አለ ን።

ሁለተኛ የነፃ ምርጫ መረጋገጥ ዋናው ዋስትናው ኢህአዴግ እነዚህን መስፈርቶች ተቀበልኩ ማለቱ ብ ቻ አይደለም። ይህ መንግስት መጭውን ምርጫ "ካለፈው በተሻለ" ሁኔታ እንዲያዘጋጅ ከባእዳን ተፅእና እየተደረገበ ት መሆኑ ያደባባይ ምስጢር ነው። በነሱ ግፊት ከተቃዋሚዎች ተደራድሬ ማሻሻያዎችን አደረኩ ለማለት ቢያንስ ቢያ ንስ ለባእዳን ፍጆታ ሲል መሰረታዊ ያልሆኑ የማዘናጊያ ለውጦችን ሊቀበል ይችላል። ግን ደግሞ ምን ያህል አሸብራቂ የሆኑ መሻሻያዎች ቢያደርግስ እነኝህን በምን ተአምር ነው እኛ አስተማማኝ አድርገን ቆጥረን ሁኔታዎች ለነፃ ምርጫ ተመቻቹ ማለት የምንችለው? ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት አለኝ፤ መድበለ ፓርቲ ስርአት አስፍኛለሁ፤ ነፃ ፕሬስን የሚ ያረጋግጥ ህግ አለ፤ የኢትዮጵያውያን የመደራጀት መብት ተረጋግጧል ወዘተ ስላለ ብቻ ዛሬ አገራችን በዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት የምትተዳደር ዴሞክራሲያዊ አገር ነች ወይ? መልሱ ግልፅ ነው።

ይህ ደግሞ ወደ ሶስተኛው ነጥባችን ያመጣናል። ለምሳሌ ባለፈው ምርጫ ኢህአዴግ አሸነፍኩ ያለው በያለበት በገፍ አጭበርብሮ ነው ብለናል። ይህ ማለት ምን ማለት ነው? የመጀመሪያው መቸስ የምርጫ ህጉ አድላዊ ነበ

ር ማለት ነው። ግን የወያኔ ማጭበርበር ዋና ገፅታ ይህ አልነበረም። አጭበርብሯል የምንለው ከራሱ የምርጫ ህግ እንፃ ር እንኳን ቢሆን ፀረ ነፃ ምርጫ "ህገ ወጥ" ርምጃዎች ወስዶ አሸንፏል ማለት እንደሆነ ግልፅ ነው። እነዚህን አንድ ሽ ገፅታ ያላቸው ማጭበርበሪያ ዘዴዎች የምናከሸፋቸው አዲስ አበባ ከነ አቶ መለስ ጋር ተደራድረን በምንፈራረማቸው ያ ሸበረቁ ሰነዶች አይደለም። እነዚህን ለመቋቋም የምንችለው ምርጫው ካምፔይን ውስጥ ስንገባ በየምርጫ ጣቢያው የ ሚፈፀሙትን ማጭበርበሮች፤ ሽፍጦች፤ አፈናዎችና ፀረ ነፃ ምርጫ ርምጃዎች ከስር ከስሩ እንደምንመዘግብና እንደም ናጋልጥ፤ በእርግጥም በስፋታቸውና በተደጋጋሚነታቸው ይህንን ምርጫ ክፉኛ የተጭበረበረ አድርገውታል የሚል ድም ዳሜ ከደረስን ደግሞ በመጨረሻው ደቂቃ የድምፅ መስጠቱን ሂደት ቦይኮት እንደምናደርግ ከወዲሁ ለሚመለከተው ሁሉ በግልፅ ስናስቀምጥ ብቻ ነው። ኢህአዴግ በድርድርና በልፈፋ ደረጃ ከሚሰጣቸው "ዋስትናዎች" ይልቅ የህዝባዊ ድላችን ማረጋገጫ አንዱ ይህ እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ በእጃችን ይዘን የምንቆየው 'ማስፈራሪያ' ካርድ ይመስለናል።

## 3ኛ. በጋራ ፕሮግራም የጋራ ተወዳዳሪዎች ማሰማራት ይኖርብናል

የብቻ ሩጫ የትም እንደማያደርስ ዛሬ ሁሉም የተገነዘበው ያፈጠጠና ያገጠጠ ሃቅ ይመስለናል። ግን ይህንን ሃ ቅ መቀበልና ከዚህ መፍለቅ ያለበትን አማራጭ ስትራቴጂ መንደፍ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እዚህም ላይ አሁን ያለው " በየምርጫ ጣቢያው አንድ ተቃዋሚ ብቻ እንዲወዳደር" የሚለው የህብረቱ አቋም አሻሚ የሆነ አቋም ነው። በጉዳ ዩ በህብረቱ ሰነድ የተጠቀመው ስትራቴጂ የሚከተለውን ይላል፤

" ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ ተቃዋሚ ድርጅቶች እንዲያቸንፉ ህብረቱ የተቃዋሚ ድርጅቶችን ተወዳዳሪዎች የውድድር ሂደት ያስተባብራል፤ ይመራል። በምርጫ ውድድሩ ወቅት በአንድ የምርጫ ጣቢያ አንድ የህ ብረቱ ተወዳዳሪ ብቻ እንዲወዳደር/እንድትወዳደር ያደርጋል።"

አሁን ባለው ሁኔታ "በአንድ የምርጫ ጣቢያ አንድ የህብረቱ ተወዳዳሪ" ማለት ጨርሶ ትርጉም የለለው ነገር ነው። ህብረቱ የድርጅቶች ህብረት ነው። የራሱ የሆኑ አባላት የሉትም። የበጎ ራእይ ሰነድ እንጂ አማራጭ የመንግስት ፕሮግራም የለውም። ለውድድሩ የሚቀርቡት የአባል ድርጅቶች አባላት ናቸው። እነዚህ ተወዳዳሪዎች ደግሞ ህዝብ ፊት ለምርጫ የሚቀርቡት የህብረቱን የጋራ ራእይ አንግበውም ቢሆን የየድርጅቶቻቸውን የፖለቲካ ፕሮግራም ይዘው ነ ው።

በዚህ ሁኔታ "በአንድ የምርጫ ጣቢያ አንድ የህብረቱ ተወዳዳሪ ብቻ" ሲባል ያለው አንድ ትርጉም አባል ድ ርጅቶችን አደራድሮና አግባብቶ በአንድ ምርጫ ጣቢያ የአንድ ድርጅት አባል ብቻ በተወዳዳሪነት የሚሰማራበትን ሁኔ ታ ያመቻቻል ማለት ብቻ ነው። በቴሌ ኮንፌራንሱ ላይ እንደታየው አንዳንዶቹ የህብረቱ አባል ድርጅቶችም የህብረቱ ን አቋም የሚተረጉሙት በዚህ መልኩ እንደሆነ ዶክተር አድማሱ በግልፅ ሲያስቀምጡት ድርጅታቸው የህብረቱን አቋ ም የተረዳው "አትሻሙ" በሚለው ትርጉሙ እንደሆነ ድርጅቶችም ጣቢያ "መሻማት" እንደሌለባቸው ከዚህ በተረፈ ግን ሁሉም የፓርቲውን ፕሮግራም አንግቦ የፓርቲውን አላማ ለህዝብ ለማስተዋወቅ ካምፔይን ማድረግ እንደሚችል ጠ ቁመዋል። ይህ አንድ አባል ድርጅት በዚህ አካባቢ የማሸነፍ እድል ካለው ሌላ አባል ድርጅት እጩውን በዚያ አካባቢ እያሰማራ የሚለው የህብረቱ የ"አትደራረሱ" ስትራቴጂ ጨርሶ የማያዋጣ አካሄድ ነው። ለምን?

አንደኛ ለምሳሌ አባል ድርጅቶች ለሃገራችን ወሳኝ በሆነው የመሬት ጥያቄ ሁሉም ተመሳሳይ አቋም የላቸውም ። የአንዳንዶቹ ፕሮግራም መሬት የግል ሃብት እንዲሆንና መሸጥ መለወጥ እንዲቻል የሚሟገት ፕሮግራም ነው። የሌ ሎች ደግሞ ይህንን አካሄድ ይቃወማል። በመሬት ፖሊሲ ጉዳይ ድርጅቶች የተለያዩ አቋሞች እንዳላቸው እየታወቀ በ ዚህ ጥያቄ ላይ በቅድሚያ አንድ የኮምፕሮማይዝ የጋራ አቋም (ማለትም አንድ የጋራ ሽግግር መንግስት የፖለቲካ ፕሮ ግራም) ሳይነደፍ የግል ሃብት የሚለው ድርጅት ደጋፊዎቹን በዚህ ጥያቄ የተለየ አቋም ለሚያራምድ ድርጅት ድምፅ እ ንዲሰጡ ከጠራ የህብረቱ አባል ድርጅቶች ወይ የየራሳቸውን ፕሮግራም፤ ወይ አንዱ የሌላውን አቋም ወይ ደግሞ ጭ ራሹን ደጋፊዎቻቸውንና ከነሱም አልፎ መራጩን ህዝብ "ሲርየስሊ" እንዳልወሰዱዋቸው የሚያሳይ አስገራሚ አካሄድ ይሆናል።

ሁለተኛ ምንም እንኳን በዚህም ቁልፍ ጥያቄ ላይ የህብረቱ አቋም ገና ግልፅ ባይሆንም "ካሸነፍን ወያኔን አስወ ግደን የጋራ ሽግግር መንግስት እናቋቁማለን" የሚል ስትራቴጂ አለን። በዚህ መልክ ተወዳድረን ከዚህ ምርጫ ስብጥር

ጥርና ተቃራኒ አቋሞች ያላቸው ተቃዋሚዎች በራሳቸው ፕሮግራምና ደጋፊዎች ብርታት ብቻ ሳይሆን የተለየ ፕሮግራም በሚያራምዱ ሃይሎችም ድጋፍ "በአሸናፊነት" ቢወጡ የሚቋቋመው መንግስት የትኛውን ፖሊሲ ይከተላል?

በኛ በኩል በአንድ ምርጫ ጣቢያ አንድ የታቃዋሚዎች ተወዳዳሪ ከሚለው አቋም ይልቅ ትግሉ "በኛና በነሱ" መሃከል እንዲሆን በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች የሃገራችን ዴሞክራቶች በሙሉ የኛ የሚሉት አንድ የጋራ ተወዳዳሪ ይኑር ብሎ በግልፅ ማስቀመጥ ሳለንበት ሁኔታ ይበልጥ ተስማሚ ስትራቴጂ ይመስለናል። ይህንን በአንድ የምርጫ ጣቢያ አንድ ሁላችንም የኛ የምንለው አንድ የህብረቱ የጋራ ተወዳዳሪ የሚል ስትራቴጂ ለመቀበል መጀመሪያውኑ በሁለት ጥያቄዎች ሳይ ግልፅ መሆንና በዚህ በኩል ጥራት ከተገኘ አንድ መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታ ማሟላት ይኖርብናል።

ግልፅ መሆን ካለባቸው ጥያቄዎች የመጀመሪያው በዚህ ምርጫ ተሳትፈንና በድል አድራጊነት ወጥተን ወያኔን የሚተካ መንግስት እናቋቁማለን ስንል ይህ የምናቋቁመው መንግስት ምን አይነት መንግስት ይሆናል? የሚለው ጥያቄ ነው። የምናቋቁመው ጊዜያዊ የዴሞክራሲ ሽግግር መንግስት እንደሆነ ሰፊ ስምምነት አለ። ይህ የጋራ የሽግግር መንግስት ወሳኝ በሆኑ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ፤ ማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ጥያቄዎች ምንም አይነት ዘላቂነት ያላቸው ውሳኔዎች የመውሰድ ስልጣን የሌለው፤ እስከተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ድረስ የሃገሪቱን አስተዳደር "አደራ" የሚባል "ኬር ቴከር ገቨርንሜንት" መልክ ይኖረዋል የሚለውም አስተሳሰብ ተቀባይነት ያለው ይመስለናል። እንዲህ አይነቱ አካሄድ ካለፈው ባገኘነው ትምህርትና ዛሬ ባለው የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ትንተና የሚታገዝ ትክክለኛ አካሄድ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፉት ሰላሳ አመታት ከንጉሱ ወደ ደርግ፤ ከደርግ ጊዜያዊ መንግስት ወደ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ፤ ከዚያ ወደ ወያኔ ሽግግር መንግስትና ወደ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ እየተባሉ በተፈራረቁበት የሽግግር ተብየ ሂደቶች ብዙ የተንከራተተ ህዝብ ነው። እነዚህ የሽግግር ወቅቶች ፀረ ህዝቦችን ብቻ ከጊዜያዊነት ወደ ቋሚ መንግስትነት እንጂ ህብረተሰባችንን በሙሉ ከፀረ ዴሞክራሲ ስርአት ወደ ዴሞክራሲ ስርአት ሳያሸጋግሩ ያለፉና የከሸፉ የጥፋት ሂደቶች ነበሩ።

ከዚህ ተገቢውን ትምህርት ከቀሰምን ከመጭው ምርጫ ሂደት የምንጠብቀው ዋና ቁም ነገር በተጨናገፈውና በከሸፈው በኢህአዴግ የሽግግር ሂደት መቃብር ሳይ አገራችንና ህዝባችን ወደ ሰላምና ዴሞክራሲ በተረጋጋ ሁኔታ የሚሸጋገሩበት ሌላ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ወቅት እንዲከፈት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

የመጭው ምርጫ ታሪካዊ ተልእኮ ይህ በመሆኑ ድርጅቶች ወገናዊ ፕሮግራማቸውን ይዘው ለህዝብ ምርጫ ለመቅረብ ከሽግግሩ ወቅት ባሻገር ብቻ የሚመጣውን ቀጣዩን ምርጫ መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ህዝባችን በተሳካ ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ዘመን አማካኝነት የተሰበጣጠሩ ድርጅቶች ከሚያቀርቧቸው አማራጮች መሃል ይሆነኛል የሚለውን ለመምረጥ የሚችልበት ደረጃ እስኪደርስ ድረስና እንዲያውም እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ዛሬ በኢህአዴግ ስታሊናዊ ህገ መንግስት የተነሳ መርጦም ምንም ለውጥ ለማያመጣበት ምርጫ አማራጮችን ማንጋጋት ምንም ፋይዳ አይኖረውም።

በዚህ ግልፅ ከሆንንና ከተስማማን ሌላ መብራራት የሚኖርበት ነጥብ "ድርጅታዊ ነፃነትን" የሚመለከተው ነጥብ ነው። የጋራ ተወዳዳሪዎች የሚለውን ሃሳብ ለጊዜውም ቢሆን በጥርጣሬ አይን የሚያዩ ወገኖቻችን የሚያነሱት ይህ ክርክር እስከዚህም አስቸጋሪ ነጥብ ሆኖ አናገኘውም። ረጋ ብለን ካየነው ጊዜያዊና የተወሰነ ታሪካዊ ተልእኮ ባለው ህብረት ውስጥ መሰባሰባችን ድርጅታዊ ነፃነታችንን አልነካውም። ህብረቱ ውስጥ የገባነው ስማችንን፤ መዋቅራችንን፤ የፖለቲካ ፕሮግራማችንን፤ የወደፊት እድላችንን እንደያዝን ነው። ምርጫው ውስጥ ስንወዳደርም ድርጅታዊ ማንነታችንን ሸሽገን አይደለም። ለአንዲት የምርጫ ወቅት፤ ለተወሰነ ታሪካዊ ተልእኮ፤ ሁላችንም በጋራ በተስማማንበት ጊዜያዊ የሽግግር መንግስት ፕሮግራም አማካኝነት ድርጅታችንን ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የሃገራችንን ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ወክለን የምንወዳደር እንደሆንና በቀጣዩ ምርጫ ግን ወገናዊ አማራጮቻችንን ይዘን እንደምንቀርብ ከወዲሁ ለህዝባችን ግልፅ አርገን የምንገባበት ሂደት ነው።

ነገሩ እንዲህ ግልፅ ሆኖ ሳለ "በድርጅታዊ ነፃነት" ሰበብ ሁሉም በየበኩሉ በመሰለው ይሂድ ማለት እንዳለፈው ምርጫ ሁሉም ድርጅት "የቻለውንና የበኩሉን" በወያኔ ፓርላማ ውስጥ ወንበር ለማግኘት ይራኮት ማለት ይሆናል። ይህ አካሄድ ደግሞ አንዱ "ከሁሉ ጎልቶ የሚታይ ተቃዋሚ ሆኖ ለመቅረብ" የሚሞክርበት አካሄድ ስለሚሆን የመጨረሻ መጨረሻ የምንወዳደረው ከወያኔ ጋር ሳይሆን እርስ በርስ የሚሆንበት አደገኛ ሁኔታ እንደሚፈጠር ቢያንስ ለኛ ግልፅ ነው። በዚህ ሁኔታ መጭውንም፤ ቀጣዩንም፤ ወዲያኛውንም ምርጫ የማሸነፍ ምንም እድል አይኖርም።

ያለውን መንግስት በምርጫ አሸንፈን ሌላ መንግስት እናቋቁማለን፤ ለዚህም በያለበት የጋራ ተወዳዳሪዎች እ ናቀርባለን ብለን ከተነሳን ደግሞ ይህንን ለማድረግ ማሟላት ያለብን ግልፅ ቅድመ ሁኔታ አለ። የጋራ የዴሞክራሲያዊ ሽ ግግር መንግስት አማራጭ ፕሮግራም ያስፈልገናል። ምርጫው እየተቃረበ ባለበት በአሁኑ ወቅት ህብረቱ ከበጎ ራእዮች ካታሎግ የዘለቀ የፖለቲካ ፕሮግራም አለው ለማለት የምንችልበት ደረጃ ላይ አይደለንም።

እርግጥ መለስተኛ የፖለቲካ ፕሮግራም ተብሎ የተሰራጨ ሰነድ አለ። ነገር ግን ነፃ ምርጫ፤ የህግ የበላይነት ፤ ነፃ ፕሬስ፤ የገበያ ኢኮኖሚ፤ የህዝቦች እኩልነትና አንድነት ወዘተ የሚሉ ወያኔ/ኢህአዴግም ቢሆን ቆሜላቸዋለሁ የ ሚላቸውንና ከፖለቲካ ፕሮግራምነት ይልቅ ወደ በጎ ራእይነት የሚያዘነብሉ መፈክሮችን ይዘን መጭው ምርጫ ካምፔ ይን ውስጥ መሳተፍ አንችልም። እንዲያውም እስካሁን የተሞከሩት የህብረትና የጋራ ትግል ሙከራዎች አንዱ ድክመ ት በራእይ ደረጃ የተንሳፈፉ አላማዎችን ብቻ አንግቦ መጓዝ ላይ ማተኮራቸው በመሆኑ ከዚህ አልፈን የጋራ የሽግግር የ መንግስት ፕሮግራም የሚነደፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርብናል። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ አላማችን "ይህንን መንግ ስት አስወግዶ በሌላና ዴሞክራሲያዊ መንግስት መተካት" ተብሎ በግልፅ በተቀመጠበት ሁኔታ ለዚህ ጥያቄ ትኩረት አ ለመስጠት በጣም ግራ የሚያጋባ አካሄድ ይሆናል። መንግስትን በመንግስት ለመተካት የሚቃጣ ሃይል አማራጭ የመንግ ስት ፕሮግራም ይዞ መንቀሳቀሱ መሰረታዊ የሆነ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ለማንም ሊሰወር የሚችል ሎጂክ አይደለም።

## 4. በተጨባጭ መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች

ከፍ ብለው በተጠቀሱት ወሳኝ ጥያቄዎች ህብረቱ ባስቸኳይ ተወያይቶ ስለመጭው ትግል ግልፅ የሆነ አቅጣ ጫ ካልያዘና አባል ድርጅቶች በሙሉ ልብ ለአንድ ግልፅ አላማ ታግለው የሚያታግሉበት ሁኔታ ካልተመቻቸ "ያለውን መንግስት በነፃ ምርጫ ተፋልሞ ለማሸነፍ" በሚል ድፍን መፈክር ብቻ ህብረቱ እንዴትና ለምን ሊቀጥል እንደሚችል አይገባንም። በደፈናውና በራእይ ደረጃ የተቀመጡ አላማዎችና ጥራት የሌላቸው ስትራቴጂዎች አሁንም እጅ ተወርች አስረውን ከፊታችን የተደቀኑትን ተጨባጭ ተግባራት እንዳናይ አርገውናል። ከነዚህ ተግባራት አንዱና የመጀመሪያው ካለንበት ውዥንብር ሰፊ ውይይት አካሂደን መውጣትና ጥራት ያለውና ለትግል የሚያመች አቋም ለሃገራችን ዴሞክራ ቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ማስጨበጥ መሆን አለበት። እዚህ ደረጃ ከደረስን የሚቀጥለው ርምጃ ምን መሆን እንዳለ በት መኢሶን እንደሚከተለው ሃሳቡን ያቀርባል፤

### 1ኛ. የዴሞክራታይዜሽንና የነፃ ምርጫ ኮሚሽን ማቋቋም

ይህ ኮሚሽን የነፃና ፍትሃዊ ምርጫ መስፈርቶችን አስመልክቶ መሰረታዊ በሆኑት ጥያቄዎች ከመንግስት ጋር የሚካሄዱትን ድርድሮች በሃላፊነት ያካሂዳል

በነዚህ ለመንግስት የሚቀርቡ መሰረታዊ ነጥቦችና በአጠቃላይ በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ጉዳይ ህዝቡ ግንዛቤዎ ች እንዲያገኝ፤ ተወዳዳሪዎችና በምርጫው ወቅት በየምርጫ ጣቢያው የተወዳዳሪዎች እማኞች ሆነው ሂደቱን የሚቆ ጣጠሩ ዜጎች መብት፤ ሃላፊነትና ተግባራት ግንዛቤ ለማስጨበጥ ስብሰባዎች ያዘጋጃል፤ ፅሁፎች ያወጣል

በነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ በዲፕሎማሲው መስክ የሚካሄዱትን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል

በምርጫው ካምፔይን ወቅት በያለበት የሚፈፀሙትን ፀረ ነፃ ምርጫ ድርጊቶች በተቀነባበረ መልክ ይሰበስባ ል፤ ይፋ ያደርጋል፤ እንዲታረሙ ህጋዊና ፖለቲካዊ ርምጃዎች ይወስዳል

በምርጫው ማብቂያ ላይ አጠቃላይ የምርጫውን ሂደት የሚገመግምና ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለአለም አ ቀፍ ኮሚኒቲው የሚቀርበውን ሪፖርት ረቂቅ ያዘጋጃል

በዚህ ግምገማ በመመርኮዝ ተቃዋሚዎች በድምፅ መስጠቱ ሂደት ይሳተፉ ወይስ ቦይኮት ያርጉ በሚለው ጥ ያቄ የውሳኔ ፕሮፖዛል ያቀርባል ወዘተ...

### 3ኛ. የሽግግር መንግስት አማራጭ ፕሮግራም አርቃቂ ኮሚቴ

ይህ ፕሮግራም በሃገራችን ዴሞክራሲን ለማስፈን ለሚያስፈልገን የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ወቅት የምንገለገል በት፤ በሚቀጥለው የ2002 እ.. ምርጫ ሁሉም ድርጅቶች የየራሳቸውን ፕሮግራም ይዘው በህዝብ ፊት መቅረብ እስኪች ሉ ድረስ መንግስት ይዘን በተግባር የምናውለው ጊዜያዊ የኮምፕሮማይዝ ፕሮግራም ነው።

በምርጫው በገፍ አጭበርብሮም ሆነ በሃቅ ተወዳድሮ ኢህአዴግ በአሸናፊነት ከወጣ ሃገራችን ይህ መንግስት ተሸንፎ ሃቀኛ የሆነ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ፈር እስክትይዝ ድረስ ህዝብ የመቀስቀሻና የማደራጃ መድረክ ሆኖ ይቀጥ ላል

ፕሮግራም አርቃቂው ኮሚቴ በየድርጅቶች የተሰየሙ አባላትና በነሱ በተጠቆሙ ከሲቪል ሶሳይቲው፤ ከታወ ቁና በየመስካቸው እውቀትና ልምድ ካካበቱ ግለሰቦች፤ ምሁራንና ፕሮፌሽናሎች የተውጣጣ ይሆናል

ፕሮግራሙን ለማርቀቅ መነሻ አድርጎ የሚነሳው የአባል ድርጅቶችን የፖለቲካ ፕሮግራም ቢሆንም ቅሉ ከነ ሱ ውጭ ያሉ የሰራተኞችና የገበሬዎች፤ የአሰሪዎች፤ የነጋዴዎችና ኢንቬስተሮች፤ የጋዜጠኞች፤ የመምህራን፤ የ ልዩ ልዩ ባለሙያዎች (ኢኮኖሚስቶች፤ የአካባቢ ጥበቃ ኤክስፐርቶች፤ የሃኪሞች በውጭ ያሉ ምሁራንና ባለሙያዎችን ወዘ ተ) የወጣቶች፤ የሴቶች፤ የሃይማኖት አባቶች ስብስቦችና ተጠሪዎችንም በማነጋገር ለአባል ድርጅቶች ረቂቅ ፕሮግራም የማቅረብ ማንዴት ይኖረዋል

በዚህ መልክ ሰፊ ውይይትና ምክክር ተደርጎበት የሚረቀው ፕሮግራም የህብረቱ አባል ድርጅቶች ተወያይተ ውበት ካፀደቁት በሁዋላ አርቃቂ ኮሚቴው የፕሮግራሙን መሰረታዊ ነጥቦችና አማራጮች በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት እ ንዲያገኙ መደረግ ስላለበት ቅስቀሳና እንቅስቃሴ ስትራቴጂ አውጥቶ ተግባራዊነቱን ይከታተላል ወዘተ....

4ኛ. የጋራ ተወዳዳሪዎች ሰያሚና አሰማሪ ኮሚቴ

እንደሳይኛው ይህም ኮሚቴ በአባል ድርጅቶች በተጠቆሙ አባላት፤ ከአባል ድርጅቶች አባልነት ያልተመዘገ ቡም ቢሆኑ በጎ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ ከሚባሉ የሲቪል ሶሳይቲው አባላት፤ ከታዋቂ ዴሞክራቶች፤ ከሃገር ሽማ ግሎች፤ ከምሁራን የተውጣጣ ይሆናል

ተወዳዳሪዎችን ለመምረጥና ለማሰማራት በመጀመሪያ የሚጠቀምበት መስፈርት የድርጅት አባልነት ቢሆንም ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ከተደራጁ ሃይሎች ብቻ በማውጣጣት የምርጫ ጣቢያዎችን በሙሉ ለመሸፈን አስቸጋሪ ስለ ሚሆንና ከዚህም በላይ ደግሞ በሙያቸውም ሆነ በህዝብ ዘንድ ባላቸው ቅባሉትና ከበሬታ ተወዳድረው በማሸነፍም ሆ ነ በአጠቃላይ ለትግሉ ሊደርጉ የሚችሉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ሆኖ ከተገኘ የጋራ ፕሮግራሙን የተቀበሉ በድርጅት ያ ልታቀፉ ዴሞክራትና አገር ወዳድ ግለሰቦችንም ለተወዳዳሪነት የመጠቆም ሃላፊነት ይኖረዋል

በዚህ መልክ የተመለመሉት ተወዳዳሪዎች ለውድድር ለመመዝገብ በሚያደርጉት ጥረት፤ ከምርጫ ቦርዱ አንፃር ማሟላት የሚኖርባቸውን ፎርማሊቲዎች በትክክል እንዲያሟሉ ምክርና እገዛ ይሰጣል፤ መዝጋቢው ባለስልጣን ሊፈጥር የሚችላቸውን መሰናክሎች ለማስወገድ ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው የዴሞክራታይዜሽንና የነፃ ምርጫ ኮሚሽን ጋር በመተባበር ይሰራል ወዘተ....

5ኛ. ሌሎች ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም

ትግላችን የሰመረ እንዲሆን ከፍ ብለው ከተጠቀሱት ኮሚቴዎች በተጨማሪ በሂደት ሌሎችም ኮሚቴዎች መመስረት እንዳለባቸው ግልፅ ነው። ከነዚህ ውስጥ ለምሳሌ የገንዘብ ሰብሳቢ ኮሚቴ ቁልፍ ሚና ከሚጠበቅባቸው ግብ ረ ሃይሎች አንዱ ነው። ከፍ ብለን የጠቀስናቸውን ተግባራት በስራ ለመተርጎም ከፈለግን በሽህ ሳይሆን በመቶ ሽህ እን ዲያውም ከዚያ በላይ የሚተመን የፋይናንስ አቅም ያስፈልገናል። ነገር ግን እንዲህ አይነት ሰፊ ድጋፍ ለመሰብሰብ ግል ፅ የሆነና ድጋፍ የሚጠየቁት ወገኖች የሚያምኑበት አቅጣጫ መነደፍ ይኖርበታል። ይህ ከመደረጉ በፊት የድጋፍ ገንዘ ብ ለመሰብሰብ የሚደረገው ጥረት ምንም የሚያረካ ካለመሆኑ በተጨማሪ አሁን እንደሚታየው የንትርክ መነሾ ስለሚሆ ን ባለንበት ደረጃ እንዲህ አይነቱ ኮሚቴ ወይም ግብረ ሃይል ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል የሚል እምነት አለን።

*የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ( መኢሶን )*
*( መጋቢት 1996 ዓ.ም.*